# የማይጋፋት ጸጋ

አገኘሁ በየነ

# መግቢያ፤

ወደ ኋላ መለስ ብለን የቤተክርስቲያንን ታሪክ በምናይበት ጊዜ የዘመነ ተሐድሶው ወቅት (The reformation era) ደምቀው ከሚታዩ የቤተክርስቲያን ታሪኮች ዋነኛ ስፍራውን ይይዛል፡፡ በዚያን ወቅት ተሐድሶአዊያኑ (The Reformers) በአንድ ድምጽ ካስተጋቡበት አስተምህሮዎች አንዱ ነው፤ የጸጋ አስተምህሮ (The doctrine of grace) ፡፡

ዛሬ ላይ እውነት ባይተዋር መኾኗ እና በርካታ ስሁት አስተምህሮዎች እና ልምምዶች የቤተክርስቲያንን ምሰባክ ተቆጣጥረው መመልከት የተለመደ ኾኗል ። ቤተክርስቲያን የእምነተ አቋሟ ኾነ የትምህርቷ መሠረተ ቅዱሳት መጽሐፍት ሲሆኑ ሲገባ የብዙዎችን ቀልብ ለመሳብ ርቱዕ አስተምህሮን አሽቀንጥራ በመጣል የነገረ መስቀሉ እውነት የሌለበት ለፍጥረታዊ ሰው የሚመች ትምህርት ላይ ትኩረት ካደረገች ውላ አድራለች ። የጸጋ አስተምህሮ ከቤተክርስቲያን ተገፍቶ እዳር ላይ ከተቀመጡ አስተምህሮዎች አንዱ ነው ። በጨለማ የሚኖር ኃጢአተኛ ሰው እግዚአብሔር በኃያል ክንዱ መድኃኒት ካላመጣለት በስተቀር አዳኙን ልያውቅ እና ሊከተለው ከቶ አይችልም ፤ ድኅነት መቶ በመቶ የእግዚአብሔር ሥራ ብቻ ነው ።

“ ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት የሚያስችል እግሮች የሌሉትን ፥ መንፈሳዊ ምሥጢራት ሊሰማ የሚችል ጆሮ የሌለውን ሰው ፥ እንዲሁም ለላየው ጨለማ ብቻ መናገር የለመደን ሰው ከነበረበት ይዞታ አውጥቶ በተቃራኒው የሚያኖር ልዑል አምላክ ካልሆነ በቀር ሌላ ማንም ሊሆን አይችልም ። ” [i]

ይህንን ሐቅ ነው ጸጋ አስተምህሮ የምያስተምረው ። በዚህች መጣጥፍ ስለ የማይጋፋት ጸጋ የማቀርብ ይሆናል ። ማብራሪያውን ከማየታችን በፊት ይህንን አስተምህሮ እንድናሰላስል ሊረዱን ከሚችሉ መዝሙሮች ውስጥ ጥቂት አዝማቾችን እና ቍጥሮችን እንመለከታለን ።

ዘማሪ ዳንኤል አምደሚካኤል በቍጥር ፩ ሰንዱቅ ከዘመራቸው መካከል ፤

*“ ድንጋዩ ልቤ ጠጣሩ ልቤ*

*መች በቀላሉ ታዛዥ ነበረ?*

*የአንተ ፍቅር ግን ውስጤን ሰበረ*

*ተረተችያለሁ ተሸንፍያለሁ*

*ኢየሱሴ ለአንተ እጅ ሰጥቻለሁ*

*ዛሬ በፍቅርህ ተማርኬያለሁ ”*

ይኸው ዘማሪ በቍጥር ፯ ሰንዱቅ ከዘመራቸው መካከል ፤

*“ ጌታ በምህረቱ ከሳበኝ ጀምሮ*

*ኢየሱስ በይቅርታው ከጠራኝ ጀምሮ*

*እርሱን እርሱን ይላል ልቤ ተቀይሮ*

*ጌታን ጌታን ይላል ልቤ ተቀይሮ ”*

ዘማሪ ወ/ሮ መንግሥቱ መና እና ውብዓለም ታደሰ በቁጥር ፩ ሰንዱቅ ከዘመሯቸው መካከል ፤

" የፍቅር ቋንቋ ልቤን ሲነካ

የሰማሁት እውነት ነፍሴን ሲያረካ

ተማርኪያለሁ {፫x}

በእጁ ገብቻያለሁ

ተማርኪያለሁ {፫x}

እጄን ሰጥቻያለሁ "

ዘማሪ አዲሱ ወርቁ በቁጥር ፪ ሰንዱቅ ከዘመሩቸው መካከል ፤

" የሕይወቴን ምዕራፍ አቅጣጫ የለወጠ

ድንጋይ ልብ ወስዶ ሥጋ ልብ የሰጠ

ድቅድቅ ጨለማ ሕይወቴን ያበራ

የእርሱን ውለታ ዳግም ዳግም ሳውራ "

ዘማሪ ዶ/ር ደረጀ ከበደ በቁጥር ፫ ሰንዱቅ ከዘመሩቸው መካከል ፤

" ለብዙ ዘመናት ሸንጬን ገትርያለሁ

ለሰበር ለደማ ለለ ለቅሜ እያየሁ

ኸይ ኸይ ... የዬ

ከእግዚአብሔር ጋር ውጊያ ምንም ዐልጠቀመኝ

እጆቼን ለነሳሁ ለዝኖ ቢማርከኝ

ኸይ ኸይ ... የዬ

ለዝማች፤

ዐይኔን ለንስቼ ጨፍኜ እንዳላይህ

በለጥንቴ ቀረሁ መነምነሉኝ ልጅህ

የምድረ በዳው ኑሮ ደበቃኛል

እጆቼን ሳንሳ ዛሬስ ማርከኸኛል

ተማርኪያለሁ

ዛሬስ ማርከኸኛል ተማርኪያለሁ

በምስራቅ ሂድ ሲለኝ ምዕራብን ስከተል

*የሰጠኸኝን ክብብ ለጥረን ጥሼ ስዘል*

*ሽይ ሽይ ... ዮዬ*

*ብዙ ተገጣጠብሉ ጠባሳ ብቻ ነኝ*

*ይቀርታው ብዙ ነው ምህረቱ ያስታመኝ*

*ሽይ ሽይ ... ዮዬ*

*ለዝማች፤*

*ዐይኔን ለንስቼ ጨፍኜ እንዳላይህ*

*በለጥንቴ ቀረሁ መነምነሉኝ ልጅህ*

*የምድሬ በዳው ኑሮ ይበቃኛል*

*እጆቼን ሳንሳ ዛሬስ ማርከሽኛል*

*ተማርክያለሁ*

*ዛሬስ ማርከሽኛል ተማርክያለሁ*

*ለዘላለም ቁጡ እንዳይሆን በእኔ ላይ*

*እግዚለብሔር ቀድሶኝ ከሰማይ*

*ሽይ ሽይ ... ዮዬ*

*እግሮቹ ስር ሆኜ ትዐዛዙን ፈጽሜ*

*ልኖር ነው ምኞቴ በቀረው ዘመኔ*

*ሽይ ሽይ ... ዮዬ*

*ለዝማች፤*

*ዐይኔን ለንስቼ ጨፍኜ እንዳላይህ*

*በለጥንቴ ቀረሁ መነምነሉኝ ልጅህ*

*የምድሬ በዳው ኑሮ ይበቃኛል*

*እጆቼን ሳንሳ ዛሬስ ማርከሽኛል*

*ተማርክያለሁ*

*ዛሬስ ማርከሽኛል ተማርክያለሁ*

*ለዳከመኝ ትግል ከማልችለው ጋሬ*

*ለቅሜን ለለማወቅ ለጉል ለንጠራራ*

*ኸደ ኸደ … ዮዬ*

*ሌልሻዳዩ ከላይ ወደ ታች እያዮኝ*

*ትጥቁ ባልቶ ለወድቅ ለዝኖ ለበለበኝ*

*ኸደ ኸደ … ዮዬ*

*ለዝማች፤*

*ዐደኔን ለንለቼ ጨፍኜ እንዳላደህ*

*በለጥንቴ ቀረሁ መነምነሉኝ ልጅህ*

*የምድረ በዳው ኑሮ ደበቃኛል*

*እጆቼን ላንሳ ዛሬለ ማርከኸኛል*

*ተማርክያለሁ*

*<u>ዛሬለ ማርከኸኛል ተማርክያለሁ</u> {፪x} ”*

ዘማሪ መጋቢ ተስፋዬ ጋቢሶ በቁጥር ፪ ለንዱቅ ከዘመራቸው መካከል ፤

*“ የሠራዊት ጌታ ኃያሉ መድኅኔ*

*ሲጠብቀን ላለ ፍርድ እና ኩነኔ*

*በኃጢአት ጣር ለኖር ተላለፊ*

*ከእለራቴ ፈታኝ መራኝ ወደ ለገሬ ”*

ዘማሪ መጋቢ ተስፋዬ ጋቢሶ በቁጥር ፫ ለንዱቅ ከዘመራቸው መካከል ፤

*“ ጊዜው ትዝ ደለናል የተጠራንበት*

*ትዳረን ሲያሸንፍ ኹሉም በያለበት*

*ሲወጣ እና ሲወርድ ለግኝተህ ለተጠራው*

*ለልማረክ ብሎ እምቢ ያለ ማነው?*

*ለዝማች፤*

*የናዝሬቱ ሊየሉለ ከእኛ ጋር ያለኸው*

*የሚናወጠውን ወጀብ በሥልጣንህ ያዘዝከው*

*ለምህ ለደጠገብም ደግመን ብንቀደለው*

*ደንቆሮዎች የነበርን መልካም ዜና ሰማን*

*ለብር እና ለወርቅ መብለጥህን ተረዳን*

*ሙታን ስታስነሳ እውር ስታበራ*

*ዓይናችን ለይቶሃል ድንቅ ሥራ ስትሠራ ”*

ዘማሪት ሶፊያ ሽባባው በቍጥር ፩ ሰንዱቅ ከዘመረችው መካከል ፤

*“ በጨለማ እያለሁ ነፍሴ ተንከራታ*

*መቼ ተውከኝ የእኔ ጌታ {፪x}*

*የሰይጣን ምርኮኛ ሆኜ የተጠቃሁ*

*ለወጣኸኝ የእኔ ጌታ {፪x}*

*ብቻዬን ሳለቅስ ሁሌ ጠዋት ማታ*

*ሰጮህ ብዬ የእኔ ጌታ {፪x}*

*ድምጼን ሰምተህ ደረስክ ሳትቆይ እስከማታ*

*አበርልኝ የእኔ ጌታ {፪x}*

*ለዝማች፤*

*እኔ ያልዘመርኩኝ ማን ይዘምርልህ ሳደረከው ነገር?*

*ለቶ እንዲህ በቀሳል ተዘርዝሮ ለያልቅም ምህረትህ ቢቁጠር*

*ትንሽ አቀለለኝ ብዬ እንጂ ለያልቅም ብዘምር ባወራ*

*ሰሳደረከው ታምር ሰሳሸጋገርከኝ ያን ኹሉ ተራራ*

*በጠሳቴ መንግሥት በእቅዱ ውስጥ ሆኜ*

*ለይተኸኛል መድኃኒቴ {፪x}*

*ለወጣኸኝ ከእጁ ሳትጠፋ ሕይወቴ*

*አበርልኝ መድኃኒቴ {፪x}*

*ልትጠቀምብኝ በእኔ ልትሠራ*

*ፈልገህ ነው የእኔ ጌታ {፪x}*

*ነጥቀህ የታደከኝ ከዚያ ባለጋራ*

*አበርልኝ የእኔ ጌታ {፪x} ”*

እነዚህን የተወሰኑ መዝሙሮችን ለአብነት ያህል ጠቀስኩ እንጂ ዘወትር የምንዘምራቸውን የጸጋ አስተምህሮን የምያንጸባርቁ በርካታ መዝሙሮችን ማቅረብ ይቻላል ።

ዛሬ በማቀርበው ጽሁፍ ከጸጋ አስተምህሮዎች ውስጥ አንዱ ስለሆነው ሰዎች ሊቋቋሙት ስለማይችሉት ጸጋ ወይም ሊጋፉት ስለማይቻል ጸጋ [1] ቅዱሳት መጻህፍትን ዋቢ በማድረግ እተታለሁ።

መልካም ንባብ!

## ማብራሪያና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት

የማይጋፉት ጸጋ፤ የሚለው ሐረግ መጽሐፍ ቅዱስ በኃጢአተኞች ድኅነት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሚሰራውን መለኮታዊ ስራ ጠቅለል ባለ መልኩ ለስምያስተምረው ትምህርት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

የሊቋቋሙት የማይችሉት ጸጋ አስተምህሮ (The doctrine of irresistible grace) እግዚአብሔር እንዲሆን ወይም እንዲከሰት የደነገገው ማንኛውም ነገር ያለ ምንም ወይም ያለ ማንም ከልካይ እንደሚሆን ( የግለሰቦች እንኳ ቢሆን እንደሚሆን ) የሚያመለክት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ በተመረጡት ሰዎች ሕይወት ውስጥ ይሰራል፡ ከዚህም የተነሳ ያለምንም ከልካይ በክርስቶስ ወደ መዳን ይመጣሉ። መንፈስ ቅዱስ ወደ ክርስቶስ በግል የሚጠራቸውን ኃጢአተኞች ወደ ድኅነት ለማምጣት በፍጹም እንደማይደክም ወይም እንደማይሳነው መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል፡፡

ሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ ይላል፡— "አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል ፥ ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም ፤ ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና፡፡ ከሰጠኝም ሁሉ አንድን ስንኳ እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሳው እንጂ የላከኝ የአብ ፈቃድ ይህ ነው ፡፡ ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው ፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሳዋለሁ፡፡ የላከኝ አብ ካላበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ። ደግሞ። ስለዚህ አልኋችሁ፥ ከአብ የተሰጠው ካልሆነ ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም አለ። " (ዮሐ. 6:37-40፣44፣65) ፡፡ ሰው በኃጢአት ከመበከሉ ወይም ከመበላሸቱ የተነሳ እግዚአብሔር ኃይሉን ተጠቅሞ በኃጢአተኛው ሕይወት ተዓምር ካልሰራ በቀር ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ ፈጽሞ አይችልም፡፡ እግዚአብሔር በመሎኮታዊ ኃይሉ ሞኝነት የሚመስለውን ነገር ግን የመዳኛ መንገድ የሆነውን የመስቀሉን ገድል በጨለመው ልባችን ካላበራ በስተቀር መዳን በፍጹም አይቻልም፤ ምክንያቱም በኃጢአት የደነከረ ማንነት ወደ እግዚአበሔር የመምጣት ፍላጎት ወይም አቅም የለውምና ።

"አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ፡ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ የድንጋዩንም ልብ ከስጋችሁ አወጣለሁ፡ የስጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ፡፡ መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ በትዕዛዜም አስሄዳችኋለሁ ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ ታደርጉትማላችሁ " — (ሕዝ. 36:26-27) ፡፡

ሰዎች እንዲሰጡ ፥ እውነትን እንድያውቁ ወይም ወደ እውነት እንዲደርሱ በትዕዛዙም እንዲሄዱ የሚያደርግ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ የትኛውም ዓይነት መልካም ስራ ከእግዚአብሔር ነው እንጂ ከሰው ክፉ ልብ ሊመነጭ ፈጽሞ አይችልም፡፡ ሐዋርያው ጳውሉስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ እንዲህ ይላል ፤ " በእናንተ መልካምን ስራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ

[1] በእንግሊዝኛ ቋንቋ " Irresistible grace " በመባል የሚታወቀውን ቃል በአማርኛ *ሊቋቋሙት የማይቻል ጸጋ* ወይም *የማይጋፉት ጸጋ* ብለን ልንተረጉመው እንችላለን ። በዚህ ጽሁፍ *የማይጋፉት ጸጋ* የሚለውን ቃል እጠቀማለሁ ።

ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼአለሁና ፤ (ፊል. 1፡6) ፡፡ በቀጣይ ምዕራፍም እንዲህ ይላል ፤ “ ስለ በጐ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሰራ እግዚአብሔር ነውና።” — (ፊል. 2፡13)

አክሎም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ድነትነት የእግዚአብሔር ብቻ ስራ እንደሆነ በ 2ጢሞ. 1፡9-10 ላይ ይናገራል፡፡ እንዲህ ይላል ፤ “ ያዳነን በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር ነውና ፥ ይህም እንደ ራሱ አሳብና ጸጋ መጠን ነው እንጂ እንደ ስራችን መጠን አይደለም፤ ይህም ጸጋ ከዘላለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን ፥ አሁን ግን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ታይቶአል ፡፡”

በዚህ አስተምህሮ ልብ ውስጥ ስሚነሱ ስሚከተሉ ጥያቄዎች መልስ አለ ፡፡

ስምንድነው አንዱ በወንጌል ስያምን ሌላኛው የማያምነው? አንዱ ከሌላው የተሻለ ፣ ምርጥ ስለሆነ ፣ የተሻለ የሥነ አመክንዮ ችሎታ ስላለው ፣ ወይም የሆነ ሌላ የወንጌል መልዕክት አስፈላጊነት እንዲያውቅ ወይም እንዲገነዘብ የሚፈቅድ ባህሪ የራሱ አድርጐ ስለሆነ ይሆን? ወይስ እግዚአብሔር በምያድናቸው ነፍሳት ውስጥ የሆነ የተለየ ነገር አድርጐ ነው? ድኅነት የምያምነው ግለሰብ በሚሰራው ስራ ከሆነ ግለሰቡ የደኅንነት ኃላፊነት አለበት፤ ከዚህም የተነሳ ሊታበይበትም ምክንያት አለው፡፡ ነገር ግን ልዩነቱ እግዚአብሔር ብቻውን በእርሱ በምያምኑና በዳኑ ሰዎች ልብ እና ሕይወት የሆነ የተለየ ነገር አድርጐ እንደሆነ ማንም ስመመካት ምንም ዓይነት ምክንያት አይኖረውም፤ ደኅንነት በእውነትም የጸጋ ስጦታ ነው ፡፡

ከላይ ላነሳነው ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ እንደሚከተለው ነው፡፡ ይኸውም መንፈስ ቅዱስ በሚድኑት ልብ ውስጥ የሆነ የተለየ ነገር ያደርጋል፤ ከዚህም የተነሳ ልባቸው ስእውነት ቃል ይከፈታል፤ በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስም ያምናሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ብቻ ሰዎችን አንደምያድን ይናገራል ፡፡

“ እንደ ምህረቱ መጠን ስአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ ፥ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም ፤” (ቲቶ 3፡5) ይላል ፡፡ በሌላ አነጋገር ወንጌልን የምያምኑና የዳኑ ሰዎች ያመኑት እና የዳኑት እንዲያው ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ስለተሰጠ ነው፡፡ የማይጋፋት ጸጋ አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱስ ፍጥረታዊውን ሰው የሚገልጸውን ያምናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ፍጥረታዊውን ሰው በኃጢአቱና በመተላለፉ ምክንያት ሙት እንደሆነ ያስተምራል፡፡

በበደላችሁ እና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ በእነርሱም ፥ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ስሚሰራው መንፈስ አለቃ እንደሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው፡፡ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሳ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን ፥ በጸጋ ድናችኋል“ — (ኤፌ. 2፡1 - 2፣5)፡፡

“ እናንተም በበደላችሁና ሥጋችሁን ባለመገረዝ ሙታን በሆናችሁ ጊዜ' ከእርሱ ጋር ሕይወትን ሰጣችሁ፤ በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ፤” — (ቈላ. 2፡13) ፡፡

ፍጥረታዊ ሰው በመንፈሱ የሞተ ወይም መንፈሳዊ ሞት የሞተ ስለሆነ የወንጌልን መልዕክት እንዲረዳና ምላሽ ይሰጥ ዘንድ አስቀድሞ ሕያው ሲሆን ወይም ዳግመኛ ሲወለድ ይገባል፡፡ ይህን በደንብ ለመረዳት ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ያስነሳበት ታሪክ ነው፡፡

በዮሐንስ ወንጌል 11፡43 ላይ ኢየሱስ አልዓዛርን " አልዓዛር ሆይ ፥ ወደ ውጭ ና " ብሎ እንደጮኸ እና አልዓዛርም ከመቃብር እንደወጣ ተዘግቦልናል፡፡ ለብዙ ቀናት ሞቶ ለቆየው አልዓዛር አስቀድሞ ምን መሆን ነበረበት? ለኢየሱስ ትዕዛዝ ምላሽ ሊሰጥ ብቁ ነበር? በፍጹም! አልዓዛር አስቀድሞ ሕያው ሲሆን ይገባል፡ ምክንያቱም የሞተ ሰው ሊሰማም ፥ ምላሽ ሊሰጥም ፈጽሞ አይችልምና፡፡

በመንፈሳዊውም እውነታው ይኸው ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደምያስተምረው በኃጢአታችን ሙታን የሆንን እኛ ለወንጌል መልዕክት ምላሽ ከመስጠታችን እና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመናችን በፊት የግድ ሕያው ልንሆን ይገባል፡፡ ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ በዮሐ. 3፡3 ላይ እንተናገረው ሰው የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማየት ዳግመኛ መወለድ አለበት፡፡ በዮሐ. 1፡12-13 ላይ ዳግመኛ መወለድ የሆነ እኛ የምናደርገው ነገር ( ከወንድ ፈቃድ የመወለድ ) ውጤት ሳይሆን የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ድርጊት እንደሆነ ተጽፏል፡፡ ልክ አልዓዛር ራሱን ወደ ሕይወት እንዳላመጣ ወይም ኢየሱስ ከሞት አስነስቶት ወደ ሕይወት ከመመለሱ በፊት ለኢየሱስ ትዕዛዝ ምላሽ መስጠት እንደማይችል ሁሉ ኃጢአተኛውም ሰው እግዚአብሔር ሕያው አድርጎት የኢየሱስንም ትዕዛዝ ሰምቶ እንዲታዘዝ ካላደረገው በስተቀር ወደ ኢየሱስ ሲመጣ በእርሱም ሊያምን ፈጽሞ አይችልም፡፡ ኤፌ. 2፡1-10 በጣም ግልጽ በሆነ መልኩ በኃጢአታችንና በበደላችን ሙታን እንደነበርንና እግዚአብሔር ሕያው እንዳደረገን ያስተምረናል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስም ደግሞ ዳግም ልደት የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ስራ እንሆነ በግልጽ ይነግረናል፡፡ ዳግመኛ ልደት ከእኛ እምነት የተነሳ የሚመጣ ሳይሆን የወንጌል መልዕክት እንድናምን የምያደርግ እግዚአብሔር የሚሰራው ስራ ነው፡፡ ይህ አስተምህሮ — ሊቋቋሙት የማይቻል ጸጋ የተባለበት ምክንያት ሁልጊዜ የታቀደለት ወይም የሚፈለገው ውጤት፡ ይኸውም የሰው መዳን ውጤት ስለሚያመጣ ነው፡፡ ዳግመኛ መወለድ ወንጌል ከማመን ተነጣጥሎ ሊታይ አይገባም፡፡ ከድኅነት ጋር የተያያዘ ማንኛውም ነገር ፥ እንድናምን የተሰጠንን እምነት ጨምሮ የእግዚአብሔር የጸጋ ስራ ነው፡፡

የእግዚአብሔር ጸጋ የማይጋፋት ጸጋ እና ውጤታማ (efficacious) የሆነበት (ሁልጊዜ የሚፈለገውን ውጤት ያመጣል) ምክንያት እግዚአብሔር " እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን ፥ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን" — (ቁላ. 1፡13) እንዲል ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት ስላፈለሰን ወይም መዝ. 3፡8 ላይ፤ " ማዳን የእግዚአብሔር ነው " ስለሚል ማዳን የጌታ ስለሆነ ነው፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቅዱሳን በጻፈው መልዕክቱ የክብሩን ዕውቀት ብርሃን የሚሰጥ በልባችንም ውስጥ በጨለማም ብርሃን ይብራ ያለው እግዚአብሔር መሆኑን ያስተምረናል፡፡

" ስለዚህ ምክንያት ምህረት እንደተሰጠን መጠን ይህ አገልግሎት ስላለን አንታክትም፡፡ ነገር ግን የሚያሳፍረውን ስውር ነገር ጥለናልና፡ በተንኰል አንመላለስም የእግዚአብሔርንም ቃል በውሸት አንቀላቅልም ፤ እውነትን በመግለጥ ግን በእግዚአብሔር

ፊት ስለው ሕሊና ሁሉ ራሳችንን እናመሰግናለን፡፡ ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ የተከደነባቸው ለሚጠፉ ነው፡፡ ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው ፥ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ፡፡ ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታ እንደሆነ እንጂ ራሳችንን አንሰብክምና ፥ ስለ ኢየሱስም ራሳችንን ለእናንተ ባርያዎች እናደርጋለን፡፡ በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን ዕውቀት ብርሃን እንዲሰጥ በልባችን ውስጥ የበራ ፡—በጨለማ ብርሃን ይብራ ያለ እግዚአብሔር ነውና ። ” — (2ቆሮ. 4:1 -6)

በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ አንዳንድ ሰዎች ወንጌልን ለምን እንደማያምኑ (ስለተከደነባቸው እና አሳባቸውም ስለታወረባቸው) ካብራራ በኋላ “ በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን ዕውቀት ብርሃን እንዲሰጥ በልባችን ውስጥ የበራ፡ በጨለማ ብርሃን ይብራ ያለ እግዚአብሔር ነውና ” በማለት ብርሃንን የሚሰጥ፣ በጨለማ የተዋጠውን ልባችንን የምያበራ፣ እርሱን እንድናውቅ የምያደርግ እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በዘፍ. 1:3 ላይ “ ... ብርሃን ይሁን፡ ... ” ያለ እግዚአብሔር ነው እርሱ ለመረጣቸው የድኅንነትን ብርሃን የሰጠ፡፡

ተመሳሳይ እውነት በተለየ ሁኔታ በሐዋርያት ሥራ 13:48 ተጽፏል፡፡ እንዲህ ይላል፤ “ አሕዛብም ሰምተው ደስ አላቸው የእግዚአብሔርንም ቃል አከበሩ ፥ ለዘላለም ሕይወትም የተዘጋጁ ሁሉ አመኑ ፤ የጌታም ቃል በአገሩ ሁሉ ተስፋፋ ። ”

እግዚአብሔር ሲያድናቸው የመረጣቸውን ያድናቸዋል፤ ስለዚህ የእርሱ የምያድነው ጸጋ ሁልጊዜ ውጤታማ ነው፡፡ ስለ እግዚአብሔር የማይጋፋት ጸጋ በ ሐዋ. 16:14 ላይ የተገለጸውን እንመልከት፡፡

“ ከትያጥሮን ከተማም የመጣች ቀይ ሐር ሻጭ እግዚአብሔርን የምታመልክ ልድያ የሚሉአት አንዲት ሴት ትሰማ ነበረች ፤ ጳውሎስም የሚናገረውን ታደምጥ ዘንድ ጌታ ልብዋን ከፈተላት ። ” — (ሐዋ. 16:14)

ጳውሎስ የሚናገረውን እውነት ልድያ ሰምታ ምላሽ እንድትሰጥ ዘንድ ልብዋን የከፈተው ጌታ እነደሆነ እና ልብዋን በመክፈት ፈገድ እርሷም ሆነች ማንም እጁ እንደሊለበት ይህ ክፍል በግልጽ ያስተምረናል፡፡

በመጨረሻም በሮሜ 8:29-30 ላይ ወርቃማ የቢዝዎት ሰንሰለት እንመለከታለን። እንዲህ ይላል፤

“ እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን። ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና፤ አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው ። ”[ii]

እዚህ እንደምናየው እግዚአብሔር ወደ ድኅነት የጠራው ሁሉ ( ውስጣዊ ጥሪ ) ይድናል ( ይጸድቃል )።

በእርግጥ ፥ የማይጋፋት ጸጋ ልብ፤ የሚለውጠው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመተላለፉ እና በኃጢአቱ ሙት የሆነን ሰው በመውሰድ መንፈሳዊ ሕይወት ይሰጠዋል ፥ ከዚህም የተነሳ የእግዚአብሔርን የድኅነት ሥጦታ የላቀ ዋጋ ያውቃል የሚል ነው ። ከዚያ በኋላ ፥ ከኃጢአት ባርነት ነጻ በመውጣቱ ያ ሰው በፈቃደኝነት ወደ ክርስቶስ ይመጣል ።

ይህን አስተምህሮ በተመለከተ ከሚነሱ የተሳሳቱ አመለካከቶች አንዱ መንፈስ ቅዱስን ፈጽሞ መቃወም ወይም ሊቃወሙት አይቻልም በማለት ያስተምራል የሚል ነው ። ሆኖም ፥ ያ አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱስ የምያስተምረው አስተምሮ አይደለም ። የእግዚአብሔርን ጸጋ ሊቃወሙት ፥ የመንፈስ ቅዱስንም ተጽዕኖ ሊቃወሙት ይችሉሉ ። ነገር ግን ፥ አስተምህሮው በትክክል የምያሳውቀው መንፈስ ቅዱስ ተቃውሞዎችን ኹሉ ማሸነፍ እንደሚችል እናም በማይጋፋት ጸጋ የተመረጡትን በመሳብ ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት እንዲወዱ እና ወንጌሉን በመረዳት እንድያምኑ ይረዳቸዋል ።

የማየጋፋት ጸጋ አስተምህሮ በቀላሉ የምያሳውቀው እግዚአብሔር ሉዓላዊ እንደሆነ እና እንደፈቃዱ ኹሉንም ተቃውሞዎች እንደምያሸንፍ መጽሐፍ ቅዱስ የምያስተምረውን ነው ። እግዚአብሔር አስቀድሞ የደነገገው ወይም የወሰነው ይሆናል ። ይህ እውነት በቅዱሳት መጻሕፍት ኹሉ ይታያል ። በ ዳን. 4፡ 35 ላይ እንዲህ ይላል፤ " በምድርም የሚኖሩ ሁሉ እንደ ምናምን ይቈጠራሉ ፤ በሰማይም ሠራዊት በምድርም ላይ በሚኖሩ መካከል እንደ ፈቃዱ ያደርጋል እጁንም የሚከለክላት ወይም ፦— ምን ታደርጋለህ? የሚለው የለም። " መዝ. 115፡3 ላይ እንዲህ ይገልጻል፤ " አምላካችንስ በላይ በሰማይ ነው ፤ በሰማይም በምድርም የፈቀደውን ሁሉ አደረገ። "

በደኅንነት ላይ የእግዚአብሔር ጸጋ የማይጋፋት ወይም ሊቋቋሙት የማይቻል ነው ፥ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሉዓላዊ ዓላማውን ወይም እቅዱን ለመፈጸም በሚወስንበት ጊዜ ማንኛውም ሰው ወይም ነገር በሚገባ ሊጋፋው ወይም ሊቋቋመው አይችልም ።

የማይጋፋት ጸጋ አስተምህሮ የምያድን እምነት ባህሪይ እንዲሁም የሰውን ደንካራ ተፈጥሮ ለማሸነፍ የግድ ምን መሆን እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ የምያስተምረውን ትምህርት በትክክል ያጠቃልልልናል ። ፍጥረታዊ ሰው በኃጢአቱ እና በመተላለፉ ሙት ስለሆነ ፥ ለውጫዊው የወንጌል ጥሪ ምላሽ ከመስጠቱ በፊት ዳግመኛ ሊወለድ ይገባዋል ። ያ እስኪሆን ድረስ ፥ ሰው የወንጌል መልዕክት እና  የእግዚአብሔርን ጸጋ ሊጋፋ ይችላል ፤ ነገር ንግ ፥ አንዴ ዳግመኛ ሊወለድ እና ወደ እግዚአብሔር የምያጋድል ልብ አሁን ሲኖረው ፥ እምነቱን በክርስቶስ ላይ እንዲያደርግ እና እንዲድን የእግዚአብሔር ጸጋ ሊጋፋ ወይም ሊቋቋም በማይችልበት ሁኔታ ይስበዋል ። እነዚህ ሁለቱ ተግባራት ( ዳግም ውልደት እና እምነት ) አንዱ ከአንዱ ሊፋቱ የማይችሉ ናቸው።

****************

**ጥያቄ ወይም አስተያየት ካሎት በሚከተሉ አድራሻዎች ያግኙ።**

- Facebook: https://www.facebook.com/profile.php?id=100063578087185
- Instagram: https://instagram.com/agegnehu.beyene?igshid=OGY3MTU3OGY1Mw==
- YouTube: https://youtube.com/@thereformation-2320?feature=shared
- Telegram: https://t.me/reformeddoctrine
- X (Twitter): https://x.com/Agegnehu_Beyene?s=09

[i] ስሜ ታደሰ ፤ የተከደነው እውነት (ገጽ 179-180)፤ አዲስ አበባ፥ ርኆቦት]